## የታሰበ የመኖሪያ አከባቢ የተፈቀደ የመኪና ማቆሚያ መርሐግብር (አር/ፒ/ፒ)

ጥቅምት 12/ 2020

### የመኖሪያ ቤቶች የተፈቀደ የመኪና ማቆሚያ ምንድነው?




የአርሊንገተን ካውንቲ የአር/ፒ/ፒ መርሐግብር የሚያገለግለው በመኖሪያ ቤቶች አከባቢ ላይ በመንገድ ዳር መኪናዎችን ለማሳረፍ የማስተዳደር ዓላማዎች ነው። ይህንንም የሚያደርገው በተመሣሣይ መንገድ ላይ ሌሎች እንዳይቆሙ በመከልከል እና አንዳንድ ሰዎችን በመንገዶች ላይ እንዲያቆሙ በመፍቀድ ነው። የየአር/ፒ/ፒ ዞኖች የሚባሉት የመኪና ማቆሚያ ፓርኪንግ ምልክት ተደርጎባቸው ይለያሉ። በካውንቲው የተሰጠ ፍቃድ እና ይለፍ ያላቸው ነዋሪዎች፣ ጎብኝዎቻቸው እና የቤት ባለቤቶች ብቻ በእነዚህ የአር/ፒ/ፒ ዞኖች ውስጥ በእነዚህ የየአር/ፒ/ፒ ገደብ ባለባቸው ሰዓታት ውስጥ (ማለትም ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋት 8 ሰዓት እስከ ምሽት 5 ሰዓት) እንዲያቆሙ ይፈቀድላቸዋል።

### የአር/ፒ/ፒ ግምገማ

ከ2017 አንስቶ የሚኖረውን ቅልጥፍና፣ የተጠቃሚዎችን ልምድ እና ፍትሐዊነትን ከግምት በማስገባት የአርሊንግተንን የአር/ፒ/ፒ መርሐግብር ተግባር እና ዓላማ የየአር/ፒ/ፒ ክለሳ መርሐግብሩ ሲገመግም ነበረ። ይህም ከ10 ዓመታት በላይ ለሚሆን ጊዜ የመርሐግብሩ አብይ የመጀመሪያ ክለሳ ነበረ። ከ2017 እ.ኤ.አ. አንስቶ ይህ ካውንቲ ማህበረሰቡን ምን ያህል እንዳሳተፈ ለመዳሰስ ያህል፥ ይህንን ማስፈንጠሪያ ይጎብኙ የመኖሪያ አካባቢ የመኪና ማቆሚያ በታ ፈቃድ ክለሳ፦ የፕሮጀክት ዝማኔ፣ የነዋሪ አመለካከት አጭር ማጠቃለያ እና ክለሳው በቀጣይነት የሚወስዳቸው እርምጃዎችየታሰበው መርሐ ግብር

በሚከተሉት ገጾች ውስጥ በአራት ርዕሶች ሆኖ የተደራጀው የታሰበ መርሐግብር ተብራርቷል፡

1. ለማመልከት የሚኖር ብቁነት
2. የፍቃድ ጣሪያ
3. ጎብኚዎች እና ሌሎች
4. ክፍያዎች

የስታፍ አባላት መርሐግብሩን የመሠረቱት ከማህበረሰቡ በሰሟቸው ነገሮች፣ ነባራዊ መርሐግብሩን በመተንተን እና ከአንዳንድ የአርሊንግተን ጎዳናዎች የተሰሰበሰቡ የመኪና ፓርኪንግ መረጃዎችን በመውሰድ ነው። የአርሊንግተን ነዋሪዎች በአር/ፒ/ፒ መርሐግብሩ ውስጥ በተለያዩ ሁኔታዎች ክፍፍል የሚታይባቸው ሲሆን አንዳንዶቹ ስለመርሐግብሩ የሚያቃርኗቸው ምክንያቶች ለአስርት ዓመታት የከረሙ ናቸው። የስታፍ አባላቶቹም ይህንን ተግዳሮት በመገንዘብ፥ የመርሐግብሩን ግቦች በማመጣጠን ለእነዚህ ችግሮች የሚሆኑ መፍትሔዎች ለመቅረጽ ሞክረዋል። የፖሊሲ አወጣጥ መርኖዎችን እና የፖሊሲ አማራጮችን በመከተል ለካውንቲው ቦርድ በኖቬምበር 2019 ላይ እንዲቀርብ ተደርጓል።

ይህ ሰነድ በታሰበው መርሐግብር እና በነባራዊው መርሐግብር መካከል ያለውን ንጽጽር ጎን ለጎን በማቅረብ ለውጦቹ ላይ ማጉያ በመጠቀም የቀረበ ቻርት ይዟል።

ስለእነዚህ ለውጦች ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገዎት፥ እነዚህ የስታፍ አባላት እንዴት ባለ ሁኔታ የታሰበው መርሐግብር ላይ እንደደረሱበት የሚከተለው አድራሻ በመሔድ ይመልከቱ፡ (በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች)

የታሰበ የአር/ፒ/ፒ መርሐግብር ከነባራዊው መርሐግብር ጋር ሲስተያይ

| የችግሩ አከባቢ | ነባራዊ መርሐግብር | የታሰበው መርሐግብር |
|---|---|---|
| **ብቁነት**<br>ለማመልከት የሚሉት ቤተሰቦች የትኞቹ ናቸው<br> | • ሁሉም ነጠላ-ቤተሰብ የተነጠሉ አባወራዎች በየተባበሩ የመኖሪያ ቤት ግንባታዎች የተገነቡ እስካሆኑ ድረስ ለማመልከት ይችላሉ<br>• አፓርታማዎች፣ ኮንዶሚኒየሞች፣ ደባሎች፣ እና የከተማ ቤት አባወራዎች ማመልከት ይችላሉ ግን<br>○ ከ1997 በኋላ የተገነቡ (ዱፕሌክስ እና የከተማ ቤቶች) ወይም ከ1964 በኋላ የተገነቡ (አፓርታማ እና ኮንዶ) መሆን የለባቸውም፤<br>○ ከየቦታ እቅድ ይሁንታ የተሰጠባቸው መሆን የለባቸውም<br>○ ከየተባበሩ የንግድ ቅይጥ አጠቃቀም ግንባታዎች ይሁንታ የተሰጠባቸው መሆን የለባቸውም<br>○ ህንጻው ነባር መኪና ማቆሚያውን የሚያስፋፋ መሆን የለበትም፤<br>○ ህንጻው ከኪራይ በተጨማሪ ለመኪና ማቆሚያ የሚያስከፍል እና ይህም በካውንቲው ከተፈቀደው የመኪና ማቆሞያ ክፍያ የሚበልጥ መሆን የለበትም፤<br>○ ህንጻው ካለበት በ2 መታጠፊያወዎች ርቀት ላይ ከመንገድ ውጭ ያለ የመኪና ማቆሚያ ቦታ ከሌላኛው ህንጻ ነዋሪዎች ጋር በመስማማት ማግኘት የሚችል መሆን የለበትም | • ሁሉም የመኖሪያ ቤች ለማመልከት ብቁ ናቸው፤ በዚህ ውስጥ የሚጨመሩት<br>○ ነጠላ ቤተሰብ የተለዩ ቤች፣<br>○ ተቀጥላ የመኖሪያ ቦታዎች<br>○ ዱፕሉክስ እና የከተማ ቤች<br>○ አፓርታማ እና ኮንዶሚኒየሞች<br>• የካውንቲው ቦርድ ከዚህ በታች በተመለከቱት አማራጮች ለልማት ያጸደቃቸው ህንጻዎች ግን ለማልከት ብቁ አይደሉም፤<br>○ የቦታ እቅድ<br>○ የተባበሩ የመኖሪያ ቤት ግንባታዎች<br>○ የተባበሩ የንግድ ቅይጥ አጠቃቀም ግንባታዎች<br>○ የንግድ ማእከላት ቅጽ ላይ የተመሰረተ ኮድ መጠቀሚያ ፍቃድ<br>○ የሰፈሮች ቅጽ ላይ የተመሰረተ ኮድ የመጠቀሚያ ፍቃድ |

| የችግሩ አከባቢ | ነባራዊ መርሐግብር | የታሰበው መርሐግብር |
|---|---|---|
| **የፍቃድ ጣሪያዎች**<br>አንድ ቤሰብ ሊያገኝ ማግኘት ያለበት የፍቃድ ልክ ምን ያህል ነው?<br> | • በአንድ ቤተሰብ ቢበዛ አራት(4) ዓመታዊ ፍቃድ የሚከተሉትን ጨምሮ፡<br>  ○ አንድ (1) ፍሌክስ ፓስ<br>  ○ ሦስት (3) ለተሽከርካሪ ተለይቶ የተሰጠ ፍቃድ (ዴካል)<br>• ነዋሪዎች ለአራት ወይም ከዚያ በላይ ለሚሆኑ ተሽከርካሪዎች እንዲፈቀድላቸው ሊያመለክቱ ይችላሉ፤ ግን እስካሁን ይህንን ያደረገ ዘን የለም<br>• በተጨማሪ መኖሪያ ክፍሎች የሚገኙ ቤተሰቦች የሚከተሉትን ሊያገኙ ይችላሉ፡<br>  ○ አንድ (1) ፍሌክስፓስ እና ከዋናው መኖሪያ የተለየ አንድ (1) የአጭር ጊዜ ጎብኚ ደብተር<br>  ○ ከፍሉክስ ፓስ ወይም ደግሞ በድምሩ አራት ከሆኑት በተለይ ለአንድ ተሽከርካሪ ከተዘጋጁት ፍቃዶች መካከል አንድ (1) እንደመንገዱ የመያዝ አቅም በማድረግ በምርጫቸው ማግኘት | ለሁሉም ቤተሰቦች በተቀጥያ መኖሪያ ክፍሎ የሚኖሩትን ጨምሮ፡-<br>• ቢበዛ ሁለት (2) ፍቃዶችን (ፍሌክስፓስን ጨምሮ) በአንድ ዓመት ለቤተሰቦቹ ይኸውም ያላቸው በመግቢያ በር፣ በጋራጅ፣ በመኪና ማረፊያ፣ ወይም በመኪና ማቆሚያ በታዎች ያለው መጠን የፈለገውን ያህል ቢሆን፤<br>• ቢበዛ ሦስት (3) ፍቃድ (ፍሌክስፓስን ጨምሮ)በአንድ ዓመት ለቤተሰቦቹ ይኸውም በመግቢያ በር፣ በጋራጅ፣ በመኪና ማረፊያ፣ ወይም በመኪና ማቆሚያ ቦታ የሌላቸው ለሆኑ፤<br>• ቤተሰቦቹ ሁሉንም ዓመታዊ ፍቃዶች በተለየ ለተሽከርካሪው ዓይነት የተለዩ አድርገው ወይም አድርገው ወይም የአንድ (1) በፍሌክስ ፓስ መልክ ለመውሰድ መምረጥ ይችላሉ፤ |
| **ጎብኚዎች እና ሌሎች**<br>ቤቶቹን የሚጎበኙ ሰዎች በአር/ፒ/ፒ ዞኖች ውስጥ የሚኖሯቸው መብቶች ምን ምን ናቸው?<br>የአር./ፒ/ፒ ገደቦች ባሉባቸው አከባቢዎች | • ለቤተሰቦች ሁለት (2) ዓይነት ፍቃድ/ይለፎች ለጎብኚዎች ተብሎ ይሰጣቸዋል፡<br>  ○ እስከ (5) ደብተሮች ባለሃያ (20) የአጭር ጊዜ ጎብኚዎች ይለፍ፤<br>  ○ አንድ (1) ፍሌክስ ፓስ፣ ፍሌክስፓስ የሚባለው ቢጠፋ የማይተካ ሲሆን፡ ከተሰረቀ ግን ይተካል፤<br>• አንድ (1) የቤት ባለቤት ፍቃድ ይለፍ በአንድ ዓመት የሚያገለግል ተደርጎ በቤቱ ለማይኖሩ ለንብረቱ ባለቤቶች ይሰጣል፤ | • ለቤተሰቦች ሁለት (2) ዓይነት ፍቃድ/ይለፎች ለጎብኚዎች እንዲጠቀሙባቸው ተብሎ ይሰጣቸዋል፡<br>  ○ እስከ (5) ደብተሮች ባለሃያ (20) የአጭር ጊዜ ጎብኚዎች ይለፍ፤<br>  ○ አንድ (1) ፍሌክስ ፓስ፣ ፍሌክስፓስ የሚባለው ቢጠፋ የማይተካ ሲሆን፡ ከተሰረቀ ግን ይተካል፤<br>• አንድ (1) የቤት ባለቤት ፍቃድ ይለፍ በአንድ ዓመት የሚያገለግል ተደርጎ በቤቱ ለማይኖሩ ለንብረቱ ባለቤቶች ይሰጣል፤ |

| የችግሩ አከባቢ | ነባራዊ መርሐግብር | የታሰበው መርሐግብር |
| --- | --- | --- |
| ሥራቸውን የሚያከናውኑ ሰዎስ ምን ይሆናሉ?<br> | • ለቤቱ በቀጥታ አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች የድርጅቶቻቸውን ዓርማ ስም (ለምሳሌFedEx, Verizon, ወዘተ) በግልጽ እንዲታይ ለጥፈው ከሆነ ገደብ አይጣልባቸውም፤<br>• ፍቃድ ለሌላቸው ሰዎች በጊዜ ገደብ የሆነ የመኪና ማቆሚያ (ይፈቀዳል ግን የተለመደ አይደለም)፤<br>• የነዋሪዎች ይለፍ የሚያስቀር ቆጣሪ (ይፈቀዳል እንጂ የለም)<br>• የጤና እና የማህበራዊ አገለግሎቶችን በአር/ፒ/ፒ ዞኖች ለሚገኙ ቤቶች ለሚያቀርቡ ድርጅቶች ሰራተኞች (ምሣ. የቤት ለቤት ጤና ድፋፍ፣ የማህበራዊ ድጋፍ ሠራተኞች፣ የቤት ኃይማኖታዊ አገልግሎት አቅራቢዎች ወዘተ) የሚሆን ለሁሉም ዞኖች የሚያገለግል ፍቃድ<br>• በአር/ፒ/ፒ ዞኖች ውስጥ ባሉ ንብረቶች ላይ ሥራ ላላቸው እና የድርጅት ዓርማ የተለጠፈበት ተሽከርካሪ ለሌላቸው የግንባታ ሥራ ተቋራጮች የሚሰጥ ጊዜያዊ ፍቃድ፤<br>• የመኪና መጋራት ተሽከርካሪዎች ከክልከላ ነጻ ቢሆኑም፥ ከ24 ሰዓታት በኋላ መነሳት አለባቸው፤ | • አንድ (1) ዓመታዊ ፍቃድ ‹‹በሁሉም ዞኖች የተፈቀደ›› ውስጥ እንዲካተቱ ለተደረጉ የትምህርት ቤት ስታፎች ይሰጣል (ከታች የተጠቀሰውን ዋቢ ያድርጉ)። በአንድ ትምህርት ቤት የሚሰጡ የፍቃዶቹ ብዛት በሚወሰን ቁጥር ልክ ጣሪያ ይበጅለታል፤<br>• አንድ (1) ዓመታዊ ፍቃድ በአር/ፒ/ፒ ዞን ውስጥ የሚገኝ በቡድን የሚኖርበት አገልግሎት መስጫ ለሚሠሩ ሰራተኞች፤<br>• የሁት ሰዓታት የሚከፈልበት የመኪ ማቆሚያከገደብ ጋር<br>  ○ የአር/ፒ/ፒ ፍቃድ ወይም ይለፍ ያላቸው ተሽከርካሪዎች ከዚህ የሁለት ሰዓት ገደብ ነጻ ናቸው፤<br>  ○ ግለሰቦች ደግሞ ክፍያቸውን በፓርክሞባይል ወይም ኢዚፓርክ ተጠቅመው መፈጸም ይችላሉ፤<br>  ○ ቆጣሪዎች አይተከሉም፤<br>• በአር/ፒ/ፒ ለሚገኙ ቤቶች በቀጥታ አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች የድርጅቶቻቸውን ዓርማ ስም (ለምሳሌፌዴክስ፣ ቨራይዘን፣ ወዘተ) በግልጽ እንዲታይ ለጥፈው ከሆነ ገደብ አይጣልባቸውም፤<br>• የጤና እና የማህበራዊ አገለግሎቶችን በአር/ፒ/ፒ ዞኖች ለሚገኙ ቤቶች ለሚያቀርቡ ድርጅቶች ሰራተኞች (ምሣ. የቤት ለቤት ጤና ድፋፍ፣ የማህበራዊ ድጋፍ ሠራተኞች፣ የቤት ኃይማኖታዊ አገልግሎት አቅራቢዎች |

| የችግሩ አከባቢ | ነባራዊ መርሐግብር | የታሰበው መርሐግብር |
|---|---|---|
| | | ወዘተ) የሚሆን ለሁሉም ዞኖች የሚያገለግል ፍቃድ ያገኛሉ<br>• በአር/ፒ/ፒ ዞኖች ውስጥ ባሉ ንብረቶች ላይ ሥራ ላላቸው እና የድርጅት ዓርማ የተለጠፈበት ተሽከርካሪ ለሌላቸው የግንባታ ሥራ ተቋራጮች የሚሰጥ ጊዜያዊ ፍቃድ፤<br>• የመኪና መጋራት ተሽከርካሪዎች ከክልከላ ነጻ ቢሆኑም፥ ከ24 ሰዓታት በኋላ መነሳት አለባቸው፤ |
| **ክፍያዎች**<br>ፍቃዶች እና ደለፎች ምን ያህል ያስከፍላሉ<br> | • ክፍያዎቹ የማስተዳደር ሥራውን እና የመርሐግብሩን አፈጻጸም 60% ያህል ወጪ ይሸፍናሉ፤<br>• ፍሌክስ ፓስረ እና የቤት ባለቤቶች ይለፎች ነጻ ናቸው፤<br>• በተለይ ለተሽከርካሪ ዓይነት የሚሰጡ ፍቃዶች፡ ለመጀመሪያው ፍቃድ $20፣ ለሁለተኛ ፍቃድ $20፣ ለሦስተኛ ፍቃድ ፪ እና ዞኑ ለተጨማሪ ፍቃዶች አገልግሎት ማመልከቻ ካቀረበ ለተከታታይ ፍቃዶች $250<br>• የአጭር ጊዜ ጎብኚች ደብተር፥ የመጀመሪያው ደብተር ነጻ ሲሆን፥ ከዚያ በኋላ ለእያንዳንዱ $5 ይከፈላል | • እነዚህ ክፍያዎች የመርሐግብሩን አስተዳደር እና አፈጻጸም ወጪዎች 100% ይሸፍናሉ፤<br>• ክፍያዎቹ በእያንዳንዱ ዓመት መርሐግብሩን በማድረሻ ወጪ ላይ ተመርኩዘው ሊጨምሩም ሆነ እንዲቀንሱ ተደርገው ሊስተካከሉ ይችላሉ።<br>• ለመጀመሪያው ዓመት<br>  ○ የፍሌክስ ፓስ እና የንብረት ባለቤት ይለፍ፡ $40<br>  ○ ለተሽከርካሪዎች ዓይነት ተለይቶ የሚሰጥ ፍቃድ፡ ለመጀመሪያው ፍቃድ $40፣ ለሁለተኛ ፍቃድ $55 እና (ሦስት ለሚገበሉ ቤተሰቦች ) ለሶስተኛው ፍቃድ $65<br>  ○ ለአጭር ጊዜ ጎብኚዎ ደብተው፥ የመጀመሪያው ደብተር $5፣ ለእያንዳንዱ ሌሎች አራት ደብተሮች $10፤<br>  ○ በሁሉም ዞኖች የሚሰራ ፍቃድ ለመስጠት፡ እያንዳንዱ $40 |

| የችግሩ አከባቢ | ነባራዊ መርሐግብር | የታሰበው መርሐግብር |
|---|---|---|
| | | ○ የትምህርት ቤት ስታፎች እና በቡድን ነዋሪዎች አገልግሎት መስጫ ስታፎች ፍቃድ፡ $40 ለእያንዳንዱ<br>○ ጊዜያዊ የሥራ ተቋራጭ ፍቃድ፡ በ$10 ክፍያ ለ3 ወራት<br>• ከሚከተሉት አጋጣሚዎች ቢያንስ አንዱ ሲያጋጥም ለፍሌክስፓስ፣ የቤት ባለቤት ይለፍ፣ በተሽከርካሪ ተለይቶ የሚሰጥ ፍቃድ፣ እና ለአጭር ጊዜ የጎብኚዎ ይለፍ ደብተር ለሚከፍሉ ቤተሰቦች የ50% ቅናሽ ይደረጋል፡<br>○ የማሟያ አመጋገብ ድጋፍ መርሐግብር (ኤን/ኤን/ኤ/ፒ) የገቡ<br>○ ሴት ጨቅላዎች እና ልጆች (ደብልዩ/አይ/ሲ)<br>○ ለተቸገሩ ሰዎች ጊዜያዊ ድጋፍ ሰጪ (ቲ/ኤ/ኤን/ኤፍ)<br>○ ኤስኤስአይ/ኤስኤስዲአይ ማሟያ የደህንነት ገቢ<br>○ የዝቅተኛ ገቢ ቤተሰብ ጉልበት ድጋፍ መርሐግብር (ኤል/አይ/ኤች/ኢ/ኤ/ፒ) ከገቡ<br>○ ሜዲኬይድ |

## ስለታሰበው ዕቅድ አስተያየት መስጫ መንገድ

በታሰበው መርሐግብር ላይ የሚኖሩ አስተያየቶች ከስታፍ አባላት ጋር በቀጥታ መስመር ላይ ባለው የግብረመልስ አድራሻ በመጠቀም ወይም በስልክ 844-568-3777 በመጠቀም እስ ከረቡዕ ኦክቶበር 28/2020 5:00 ፒኤም ድረስ መስጠት ይቻላል። እባክዎን ግብረመልስ የሚሰጡበትን መንገድ

በተመለከተ እና ስለታሰበው መርሐግብር የሚጨምሩት ነገር ቢኖር ይበልጥ ዝርዝሮችን ማግኘት የሚከተለውን የድረገጽ አድራሻ ይጎብኙ፡ (በመኖሪያ አካባቢ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ፈቃድ (RPP) ክለሳ)